# የሀጅ እና ኡምራ መመሪያ



## ኡምራህ

### 1. ሚቃት ከመድረስዎት በፊት ኢህራም ያድርጉ

#### ከኢህራም በፊት



የሚይፈለግ ፀጉር ያስወግዱ፡፡ ጥፍርዎትን ይቁረጡ፣ ገላዎትን ታጥበው ወዱእ ያድርጉ ወይም ቢያንስ ወዱእ ብቻ ያድርጉ፡፡ የኢህራም ጨርቆችን ይልበሱ፡፡ ሁለት ያልተሰፉ ጨርቆችን ለወንዶች ለሴቶች ደግሞ መደበኛ (የአዘቦት ቀን) ልብስ፡፡ በኢህራም ጊዜ ሴቶች ፊታቸውን ወንዶች ደግሞ ጭንቅላታቸውን መሸፈን የለባቸውም፡፡

**ኢህራም ሲያደርጉ**

ኢህራም ማድረግዎትን በማንኛውም ቋንቋ ይነይቱ ወይም የሚከተለውን ይበሉ፡፡

**لَبَّيْكَ اللَّهُمَّ بِعُمْرَةَ**

**ለበይክ አላሁመ ቢኡምራህ**

አላህ ሆይ የኡምራህ ትዕዛዝህን ለሟሟላት (እዚህ ተገኝቼ) አቤት ብያለሁ ተቀበለኝ

ወደ ማስጂደል ሀረም (ካዕባህ) በሜድ ወንዶች ጮክ ብለው ሴቶች ደግሞ በቀስታ የሚከተለውን ተልቢያህ ይላሉ፡፡

**لَبَّيْكَ اللَّهُمَّ لَبَّيْك، لَبَّيْكَ لاَ شَرِيْكَ لَكَ لَبَّيْك،**
**إِنَّ الْحَمْدَ وَ النِّعْمَةَ لَكَ وَ الْمُلْكُ لاَ شَرِيْكَ لَك**

**ለበይክ አሏሁመ ለበይክ ለበይክ ላሸሪከ ለከ ለበይክ ኢነልሀምዷ ወኒዕመተ ለከ ወልሙልኩ ላሸሪከለከ**

አቤት አላህ ሆይ አቤት ፣ አቤት ለአንተ ሸሪክ የለህም ፣ አቤት ምስጋና፣ ፀጋና ንግስና ለአንተ ብቻ ናቸው፡ የሚጋራህ የለም፡፡

**ኡምራህ (ጠዋፉልቁዱም)**

**በመካ የሚገኘውን ማስጂደል ሀረም (ቅዱስ ማጊድ) መግባት**

በቀኝ እግርዎት በመግባት የሚከተለውን ይበሉ፡፡

**اللَّهُمَّ افْتَحْ لِي أَبْوَابَ رَحْمَتِكَ**

**አሏሁ መፍተህ ሊ አብዋበ ረህመቲከ**

አላህ ሆይ የእዝነት በርህን ክፈትልኝ፡፡

- ለጠዋፍ ይነይቱ፡፡

### 2. ጠዋፍ (ካዕባን ሰባት ጊዜ መዞር)

ወደ ጠዋፍ መጀመሪያ ቦታ ማለትም አልሀጀሩል አስወድ (ጥቁሩ ድንጋይ) ከሜድዎት በፊት




- **ወንዶች ብቻ:** ኢህራሙን በቀኝ ብብት ወስጥ
- በማድረግ ቀኝ ትከሻዎትን ይግለጡ (ይህም ኢድቲባ በመባል ይታወቃል)፡፡ **እንንዳንዱን ዙር ሲጀምሩ**
- በቀኝ እጅዎት ወደ ሀጀሩ ልአስወድ (ጥቁሩ ድንጋይ) በማመላከት የሚከተለውን ይበሉ፡፡
-

**اللَّهُ أَكْبَر**

**አሏሁ አከበር**

(አሏህ በጣም ትልቅ ነው፡፡)

ከታቻለ በሀጀሩ ልአስወድ (ጥቁሩ ድንጋይ) ማእዘን እና በበሩ ማሃል ያለዉን ቦታ ይቀፉት፡፡
ወንዶች በመጀምሪያዎቹ ሶስት ዙሮች ብቻ በፍጥነት (ረምል) መራመድ ይችላሉ፡፡ ቀሪዎቹ አራቱ ዙሮች እስከ ሰባተኛው ዙር አካባቢ በኖርማል (በተለመደው) የእርምጃ ፍጥነት ይካሄዳሉ፡፡ ለጠዋፍ የተለየ ዱዓ አያስፈልገውም ፡(ከየመን ማእዘን እስከ ጥቁሩ ድንጋይ ባለው ቦታ ማሃል እንደሚባል ከጠቀስነው በቀር በካዕባ ዙሪያ ሲኬድ የሚደረግ የተለየ ዱዓ የለም፡ ስለዚህም ደስ ያለዎትን ቁርአን መቅራት ወይም ደስ ያለዎትን ዱዓ ማድረግ ይችላሉ)፡፡

- በጠዋፍ ጊዜ ዱዓ ሊደረግ ይችላል፡፡ ነገር ግን በአሩክኑል የመኒ መሃል ስናልፍ የሚከተለውን ማለት ይወደዳል፡፡[4]



**رَبَّنَا آتِنَا فِي الدُّنْيَا حَسَنَةً وَ فِي الآخِرَةِ حَسَنَةً وَ قِنَا عَذَابَ النَّار**

**ረበና አቲና ፊዱንያ ሀሰነተን ወ ፊል አኺረቲ ሀሰነተን ወቂና ዓዘበናር**

ጌታችን! በአዱንያም በአኺራም ደህና ነገር ስጠን፡፡ ከተቻለ አሩክኑል የሚን በያንዳንዱ ጊዜ ይንኩት (ነገር ግን አይሳሙት)፡ ይህም በጣም ተመራጭ ነው፡ ካልሆነ ግን ወደሡ በጣትዎ አያመላክቱ፡፡

- ጠዋፍ ሲጠናቀቅ ቀኝ ትከሻዎትን ይሸፍኑ እና ከኢብራሂም ጣቢያ በስተጀርባ ባለው ማንኛውም ቦታ ወይም ሀረም ወስጥ በሚገኝ ማንኛውም ቦታ 2 ረከዓ ይስገዱ ሡረቱል ካፊሩን በመጀመሪያው ረከዓ እና ሡረቱል ኢኽላስ በሁለተኛው ረከዓ ይቅሩ፡፡
- የዘምዝም ወሃን ይጠጡ፡ ከዛም ዱዓ ያድርጉ፡፡

### 3. ሠዕይ (ሰፋ እና ሜርዋህን ሰባት ዙር ማጠናቀቅ)




ሠዕይን አሡፋ ላይ ይጀምሩ፡ ፡ከአሰፋ እስከ አልመርዋህ ያለውን ጉዞ (አንድ ዙር) ያጠናቅቁ፡፡ ከዛም ከአልመርዋህ እስከ አሰፋ ያለውን (ሁለተኛ ዙር)፤ ከዛም አልመርዋህ ላይ እስኪጨርሱ ድረስ ሰባቱን ዙር ይቀጥሉ፡፡ **ለወንዶች ብቻ:** አረንጓዴ መብራቶች ሲያጋጥምዎት ከአንዱ መብራት ወደ ሌላው መብራት ይሩጡ፡ በአሡፋ ስር የሚከተለውን ይበሉ፡፡

**إِنَّ الصَّفَا وَالْمَرْوَةَ مِنْ شَعَآئِرِ اللَّهِ فَمَنْ حَجَّ الْبَيْتَ أَوِ اعْتَمَرَ فَلاَ جُنَاحَ عَلَيْهِ أَنْ يَطَّوَّفَ بِهِمَا وَمَنْ تَطَوَّعَ خَيْراً فَإِنَّ اللَّهَ شَاكِرٌ عَلِيْم**

**ኢነሡፋ ወልመርወት ሚን ሸዓኢሪላሂ ፈመን ሀጀልበይተ አዊዕተመረ ፈላ ጁናሀ ዓለይሂ አንየጠወፈ ቢሂማ ወመንተጠወዐ ኸይረን ፈኢነሏህ ሻኪሩን ዓሊሙን**

አሰፋ እና አልመርዋህ የአሏህ ምልክቶች ናቸው፡ ስለዚህም ሀጅ ወይም የቤቱን ኡምራህ የሚያካሂድ ሠው በነሡ ማሃል ጠዋፍ ቢያደርግ ወንጀል አይሆንበትም፡

**اللَّهُ أَكْبَر، اَللَّهُ أَكْبَر، اَللَّهُ أَكْبَر**
**لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ وَحْدَهُ لاَ شَرِيْكَ لَه، لَهُ الْمُلْكُ وَ لَهُ الْحَمْدُ يُحْيِي وَ يُمِيْتُ وَ هُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيْر؛ لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ وَحْدَهُ لاَ شَرِيْكَ لَه، أَنْجَزَ وَعْدَهُ وَ نَصَرَ عَبْدَهُ وَ هَزَمَ الأَحْزَابَ وَ حْدَه**

**አሏሁ አክብር አሏሁ አክብር አሏሁ አክብር ላኢላሃ ኢለሏህ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሀምድ ዩህዪ ወዩሚት ወሁወ ዓላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር፡ ላኢላሃኢለሏህ ወህደሁ ላሸሪከለሁ አንጀዘ ወዕደሁ ወነሰረ ዓብደሁ ወሀዘሚልአሕዛበ ወሕደሁ**

አሏህ በጣም ትልቅ ነው አሏህ በጣም ትልቅ ነው አሏህ በጣም ትልቅ ነው ከአሏህ በስተቀር ሊገዙት የሚገባ ምንም ነገር የለም፡፡ እሱም ብቸኛ እና ሸሪክ የለውም፡፡ ሁሉም ምስጋና እና ንግስና ለእሱ ብቻ ነው፡ እሱ ብቻ ህይወት ይሠጣል ሞትም ያመጣል፡፡ ሁሉንም ነገር ማድረግ ይችላል፡፡ ከአሏህ በቀር ሊገዙት የሚገባ ምንም ነገር የለም እሱም ብቸኛና አጋር የሌለው ነው፡ ቃሉን ፈፀመ አገልጋዩንም ረዳ እሱም ብቻውን የአህዛብን ሰራዊት አሸነፈ፡፡

### 4. ፀጉርን መላጨት ወይም ማርከም

ሰዕይን ካጠናቀቁ በኃላ **ወንዶች:** ጭንቅላትን በሙሉ መላጨት ይወደዳል ወይም በጭንቅላት ላይ ያለውን ፀጉር በሙሉ እኩል አድርጎ ማርከም፡፡ **ሴቶች:** ደግሞ የጣትን አንድ ሶስተኛ (ሲሶ) የሚሆን ፀጉር መቁረጥ፡፡
ከመስጂዱል ሀረም በግራ እግርዎት ሲወጡ የሚከተለውን ይበሉ፡፡

**اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ مِنْ فَضْلِك**

**አሏሁመ ኢኒ አስአሉከ ሚን ፈድሊከ**

አሏህ ሆይ ከትርፋትህ እጠይቃለሁ፡፡

አሁን ሁሉም የኢህራም ክልክሎች በማሳታቸው ኢህራም ያስወግዱ፡፡ ኡምራ አሁን በማጠናቁ የዙልሂጃን 8ኛው ቀን ጠዋት ይጠብቁ ፡፡

**መዲናን፣ ማስጅድ አልነበዊን፣ ማስጅድ ቁባን መጎብኘት**

ለሀጅም ይሁን ለኡምራህ መዲናን መጎብኘቱ አስገዳጅ አይደለም፡፡ ነገር ግን አልማስጂደል ነበዊን (የነቢያችንን ማስጂድ) መጎብኘቱ ትልቅ ዋጋ አለው፡ ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡፡«በዚህ በእኔ ማስጊድ (መዲና) ወስጥ የሚሰገድ አንድ ሰላት በማስጂደል ሀረም (መካህ) ከሚሰገደው በስተቀር ሌላ ቦታ ከሚሰገደው በ1000(አንድ ሺህ) ሰላት ይበልጣል፡፡ በማስጂደል ሀረም የሚሰገድ አንድ ሰላት ደግሞ ሌላ ቦታ ከሚሰገደው በ100,000(መቶ ሺህ) ሰላት ይበልጣል››፡፡
ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንደዚህም ብለዋል፡ ‹‹ማንኛውም እቤቱ ወዱእ አድርጎ በማስጂድ ቁባ (በእስልምና ታሪክ የተገነባ የመጀመሪያው ማስጂድ) የሚሰግድ ሰው የኡምራህን ያህል ምንዳ ያገኛል››፡፡

**የሀጅ አይነቶች**

ማንኛውም ሀጅ ማድረግ የፈለገ ሰው ከሚከተሉት ሶስት የሀጅ አይነቶች አንዱን ይመርጣል፡፡

- **ተመቱእ:** ኡምራህን ከዛም ሀጅን በተጠቀሱት የሀጅ ወራት ማድረግ፡፡ ይህም ከሶስቱ የሀጅ አይነቶች ምርጥ ተደርጎ የሚቆጠር እና ነቢዩ ሙሃመድ (ሠ.ዐ.ወ) ተከታዮቻቸው እንዲያደርጉት አጥብቀው የመከሩበት የሀጅ አይነት ነው፡፡
- **ቂራን:** ኡምራህ እና ሀጅን በተመሳሳይ ጊዜ ማድረግ
- **ኢፍራድ:** ሀጅን ብቻ (ያለኡምራህ) ማድረግ፡፡ ተመቱእ ወይም ቂራንን ከመረጡ ኡድሂያ (በግ ማረድ) ይኖርብዎታል፡፡ **የሚከተሉትን ማድረግዎትን እንደይረሱ**
- እዳዎትን በሙሉ መክፈልዎትን
- ላጠፉት ጥፋት ማካካሻ ማድረግዎትን
- ኑዛዜ መፃፍዎትን

For more copies:

The Islamic Bulletin
PO Box 410186 SF CA 94141
USA
♦E-Mail: info@islamicbulletin.org
♦Web: www.islamicbulletin.org

Amharic አማርኛ الأمهرية، إثيوبيا
رقم اذن بطبع ٥٢٠٩/م /ج في ٣٠ / ١٢/ ١٤٣١



# ሀጅ

## የህይወት ዘመን ጉዞ

| | | |
|---|---|---|
| መካ ሲደርሱ | - | ጠዋፍ ማድረግ |
| የዙልሂጃ 8ኛወቀን | - | ኢህራም መልበስ |
| | | ሚና ይቆዩ |
| የዙልሂጃ 9ኛወቀን | - | አረፋ ይቆዩ |
| | | ሙዝደሊፋ ይቆዩ |
| የዙልሂጃ 10ኛው ቀን | - | ቋሚዎቹ ላይ ጠጠርመወርወር |
| | | ኡድሂያ ማድረግ (በግ ማረድ) |
| | | ፀጉር መላጨት |
| | | ጠዋፉል ኢፋዳህ |
| የዙልሂጃህ11ኛው 12ኛእና 13ኛወቀን | - | ድንጋይ ለመወርወር ሚና ይቆዩ |
| ከመካ ሲወጡ | - | ጠዋፉል ወዳዕ ያድርጉ |

## የዙልሂጃ 8ኛው ቀን (የወሙተርዊያህ)

ካሉበት ቦታ ሆነው ሆቴልም ይሁን ቤት ወይም ሌላ ነገር ኢህራም ያድርጉ የሚከተለውን በማለት ይነይቱ:

**لَبَّيْكَ اللَّهُمَّ بِحَجّ**

**ለበይክ አሏሁመ ቢሀጀህ**

አላህ ሆይ የሃጅ ትዕዛዝህን ለማሟላት (እዚህ ተገኝቼ) አቤት ብያለሁ ተቀበለኝ

ፊትዎትን ወደ ቂብላ አቅጣጫ በማድረግ ተልቢያህ ይበሉ፡፡

**لَبَّيْكَ اللَّهُمَّ لَبَّيْك، لَبَّيْكَ لاَ شَرِيْكَ لَكَ لَبَّيْك،**
**إِنَّ الْحَمْدَ وَ النِّعْمَةَ لَكَ وَ الْمُلْكُ لاَ شَرِيْكَ لَك**

**ለበይክ አሏሁመ ለበይክ ለበይክ ላሸሪከ ለከ ለበይክ ኢነልሀምደ ወኒዕመተ ለከ ወልሙልኩ ላሸሪከለከ**

♦አቤት አላህ ሆይ አቤት ፣ አቤት ለአንተ ሸሪክ የለህም ፣ አቤት ምስጋና፣ ፀጋና ንግስና ለአንተ ብቻ ናቸው፡፡ የሚጋራህ የለም፡፡

ከፈጅር ቡኃላ እና ከዙሁር በፊት ባለው ወቅት መሃል ወደ ሚና ይሂዱ (ጠዋት ቢሆን ይመረጣል)፡፡

**ሚና ይቆዩ**



ዙሁር፣ ዓስር፣ መግሪብ እና ዒሻእ ሠላትን ሚና ይስገዱ፡፡ለዙህር ፣ አስር፣ እና ኢሻዕ ለያንዳንዳቸው ሁለት ፈርድ ይስገዱ መግሪብ አያጥርም፣ ሶስት ፈርድ እንደሆነ ይቀራል፡፡ ከኢሻእ በኃላ ዊትር ይከተላል፡፡

ሙሉ ቀን ዒባዳ ያድርጉ (አላህን ይገዙ)፡፡

## የዙልሂጃህ ዘጠነኛው ቀን

### ዓረፋ ይቆዩ



- የፈጅር ሰላት ሚና ይስገዱ፡፡
- ፀሀይ ከወጣች በኃላ ባለው ማንኛውም ጊዜ አረፋት ይሂዱ፡፡ ከታቻለ ነሚራህ (አረፋህ አጠገብ የሚገኝ እና አሁን ማስጊድ ያለበት ቦታ) ይረፉ፡፡ ከዘዋል (እኩል ቀን በኃላ) እስካለው ጊዜ በመቆየት ኹጥባ ያዳምጡ፡፡ ይህም ካልተቻለ ወደ አረፋህ መቀጠል እና ፀሀይ እስከምትጠልቅ ድረስ እዛው መቆየት ይፈቀዳል ፡፡ በእዝነት ተራራ (ጀበሉ ረህማ) ስር በሚገኙ ድንጋዮች ላይ ይቁሙ፡፡ ካልሆነም አረፋህ በሙሉ የመቆሚያ ቦታ ነው፡፡ ፊትዎትን ወደ ቂብላ በማዞር፣ እጅዎትን ከፍ አድርገው ዱዓ ያድርጉ ተልቢያህም ይበሉ፡፡ የሚከተለውን ደጋግሞ ማለት ይወዳዳል፡፡

**لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ وَحْدَهُ لاَ شَرِيْكَ لَه، لَهُ الْمُلْك،**
**وَ لَهُ الْحَمْد، وَ هُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيْر**

**ላኢላሃ ኢላሏሁ ወህደሁ ላሸሪክለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሀምዱ ወሁወ ዓላኩሊ ሸይኢንቀዲር**

ከአላህ በስተቀር በእውነት ሊገዙት (ሊያመልኩት) የሚገባ የለም፡፡ እሱም ብቸኛ እና ሸሪክ የሌለው ነው፡፡ ሁሉም ነገር፣ ሁሉም ምስጋና የሱ ነው፡ እሱም በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው፡፡

ይህም በዚህ ታላቅ ቀን የሚደረግ ምርጥ ዱዓ ነው፡፡ አረፋ ላይ ዙሁር እና ዓሰር ይስገዱ፡፡ወቁፍ ያድርጉ (ቆመው ይስገዱ)፣ ዱዓ ያድርጉ፣ ፀሀይ እስከትጠልቅ እስቲግፋር ያድርጉ(የአላህን ምህረትይጠይቁ)፡፡ፀሀይ ከጠለቀች በኃላ መዝደሊፋ ይሄዱ፡፡

### መዝደሊፋ ይቆዩ፡፡

መዝደሊፋ ላይ መግሪብ እና ኢሻዕን አንድ ላይ ይስገዱ፡፡ ኢሻዕ ሁለት ፈርድ ይስገዱ መግሪብ አያጥርም፣ ሶስት ፈርድ እንደሆነ ይቀራል፡፡ ከኢሻእ በኃላ ዊትር ይከተላል፡፡፡ የሚወረወሯቸውን 70 ጠጠሮች ከሙዝደሊፋ ወይም ሚና ይልቀሙ ሁሉም በመጠን ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ጠጠሮቹን ከሚናም መልቀም ይችላሉ፡፡ ለ10ኛው ቀን 7 ጠጠር ብቻ ያስፈልግዎታል፡፡ ከዛ በኃላ ግን 42 (በድምሩ 49) ያስፈልግዎታል፡፡ ለ13ኛው ዙልሂጃ የሚቆዩ ከሆነ ግን ተጨማሪ 21 ጠጠር (በድምሩ 70) ያስፈልግዎታል፡፡ የጠጠሮቹ ማጠን ከሽንብራ መብለጥ የለበትም (በግምት 1 ሴ.ሜ.ወይም 0.39 ኢንች)፡፡ ለሊቱን በኢባዳ (አላህን በመገዛት) ያሳልፉ ወይም እስከፈጅር ድረስ ይተኙ፡፡

## የዙልሂጃ 10ኛው ቀን



- የፈጅር ሰላት መዝደሊፋ ይስገዱ፡፡
- ከፈጅር በኃላ ወደ ሚና ይሂዱ፡፡ ፀሀይ ከጠለቀች በኃላ እስከ ለሊት ባለው ጊዜ ጠጠር ለመወርወር ወደ ጀመረቱል ዓቀባህ አልኩብራ በፀጥታ ይሂዱ፡፡ መካን በግራዎት በኩል፣ ሚናን በቀኝዎት በኩል በማድረግ እና ፊትዎትን ወደ ጀምራህ በማዞር የሚከተለውን እያሉ ሰባት ጠጠሮች ይወርወሩ፡፡

**اللّٰهُ أَكْبَر**

**አሏህ አክብር**

አሏህ በጣም ትልቅ ነው (እያንዳንዱን ጠጠር ከወረወሩ ቡኃላ) ፡፡



**ኡድሂያ ማድረግ (በግ ሚድ)** የእርድ ትኬት ከተገዛ ይህ የሚበቃ አማራጭ ነው፡፡ ያበለዚያ እርድ ለሚፈፀም ሚና ወደሚገኘው የእርድ ቤት (ቄራ) በፀጥታ ይሂዱ፡፡ **ከእርድ ቡኃላ** ፀጉርዎትን ይላጩ ወይም ይከርከሙ **ወንዶች**፡ ፀጉር መላጩ ይወደዳል አለበለዚያም ጭንቅላትዎ ላይ የሚገኘውን ፀጉር በሙሉ እኩል አድርገው ይስተካከሉ ፡፡

**ሴቶች**፡ የጣት አንድ ሶስተኛ (ሲሶ) ያህል ፀጉር ይቁረጡ፡ አሁን ሁሉም ክልክሎች በመሳታቸው ኢህራም ያንሱ፡፡ ጠዋፉል ኢፋዳህ ለማድረግ ወደ መካ ይሂዱ፡፡

♦**ሴቶች**፡✂.

የጣት አንድ ሶስተኛ (ሲሶ) ያህል ፀጉር ይቁረጡ፡ አሁን ሁሉም ክልክሎች በመሳታቸው ኢህራም ያንሱ፡፡ ጠዋፉል ኢፋዳህ ለማድረግ ወደ መካ ይሂዱ፡

### ጠዋፉል ኢፋዳህ



ወደ መካ ሄደው ጠዋፉል ኢፋዳህ ያድርጉ፡፡ ይህም በዙልሂጃ 12ኛው ቀን ፀሀይ እስከትጠልቅ ድረስ ሊደረግ ይችላል፡፡ ማስጂዱል ሀረምን በቀኝ እግርዎት በመግባት ማስጂድ ሲገባ የሚደረገውን ዱኣ ያድርጉ፡፡ (የኡምራውን ክፍል ይመልከቱ)፡፡ ኢህራም አያስፈልግም፡፡ ከሀጀሩል አስወድ (ጥቁሩ ድንጋይ) ይጀምሩ፡፡

- ጠዋፍ ሲጠናቀቅ ከኢብራሐም ጣቢያ በስተጀርባ ባለ ማንኛውም ቦታ ሁለት ረከዓ ይስገዱ፡፡ ወይም ሀረም ወስጥ በሚገኝ ማንኛውም ቦታ በ1ኛው ረከዓ ሱረቱል ካፊሩን በ2ኛው ረከዓ ደግሞ ሱረቱል ኢኽላስ ይቅሩ፡፡
- የዘምዘም ወሃን ይጠጡ ዱዓም ያድርጉ፡፡
- ሰዕይ ያድርጉ (የኡምራውን ክፍል ይመልከቱ)፡፡ ሠዕይን በማጠናቀቅዎ፣ ሁሉም ክልክሎች አሁን ተነስተዋል፡፡
- ወደ ሚና ይመለሱ፡፡
- ከማስጂዱል ሀረም በግራ እግርዎት ሲወጡ ከማስጊድ ሲወጣ የሚባለውን ዱኣ ያድርጉ፡፡ (የኡምራውን ክፍል ይመልከቱ)፡፡



## የዙልሂጃህ አስራአንደኛው ቀን

በ10ኛው ቀን ጠዋፉል ኢፋዳህ ካላደረጉ፣ ❸❷❶ ወደ መካ ሄደው ጠዋፍ ያድርጉ፡ ፡፡ከዛም 2 ረከዓ ይስገዱ፣ ከዘምዘም ይጠጡ እና ሰእይ ያድርጉ፡፡ ከዛም ወደ ሚና ይመለሱ፡፡ ሴቶች የወር አበባ በሚያጋጥማቸው ጊዜ በመካ ለጠዋፍ ተጨማሪ ቀን መመደብ ይኖርባቸዋል፡፡

**ጠጠር ለመወርወር ሚና ይቆዩ** ከዘዋል (ከእኩለ ቀን በኃላ ያለው ጊዜ) ቡኃላ እና ለሊት መሃል ባለው ጊዜ ሶስቱም ጀመራት ላይ ጠጠር ይወርውሩ፡፡ በቀን 21 ያስፈልጋል፡፡❸❷❶



መካን በግራዎት በኩል፣ ሚናን በቀኝዎት በኩል እና ፊትዎትን ወደ መጀመሪያው ጀመራህ(በጣም ትንሹ) በማድረግ የሚከተለውን እያሉ ከሰባቱ ጠጠሮች ወስጥ እያንዳንዱን ጀመራህ ላይ ይወርወሩ፡፡

**اللّٰهُ أَكْبَر**

**አሏህ አክበር**

አሏህ በጣም ትልቅ ነው ❶ (እያንዳንዱን ጠጠር ከወረወሩ በኃላ)፡፡ በመጀመሪያው ጀመራህ ከወረወሩ በኃላ የመጀመሪያውን ጀመራህ በቀኝዎት በኩል በማድረግ ፊትዎትን ወደ ቂብላ በማዞር እና እጅዎትን በማንሳት የፈለጉትን ዱዓ ያድረጉ፡፡ ከዛም በፀጥታ ወደ ሁለተኛው (የመሃከለኛው)❷ ጀመራህ ይቀጥሉ፡፡ ፊትዎትን ወደ ሁለተኛው ጀመራህ፣ መካን በግራዎት በኩል እና ሚናን በቀኝዎት በኩል በማድረግ የሚከተለውን እያሉ ከሰባቱ ጠጠሮች እያንዳንዱን ጀመራህ ላይ ይወርወሩ፡፡

**اللّٰهُ أَكْبَر**

**አሏሁ አከበር**

አሏህ በጣም ትልቅ ነው (እያንዳንዱን ጠጠር ከወረወሩ ቡኃላ)፡፡ ሁለተኛው ጀመራህ ላይ ጠጠር ከወረወሩ ቡኃላ ፊትዎትን ወደ ቂብላ (ሁለተኛውን ጀመራህ በቀኝዎት በኩል) በማድረግ እጅዎትን አንስተው የፈለጉትን ዱዓ ያድርጉ፡፡ ከዛም በፀጥታ ወደ ሶስተኛው ጀመራህ (አልአቃባህ አልኩብራ) ይቀጥሉ፡፡ ❸ ፊትዎትን ወደ 3ኛው ጀመራህ፣ መካን በግራዎት በኩል፣ እና ሚናን በቀኝዎት በኩል፣ በማድረግ የሚከተለውን እያሉ ከሰባቱ ጠጠሮች ወስጥ እያንዳንዱን ጀመራህ ላይ ይወርወሩ፡፡

**اللّٰهُ أَكْبَر**

**አሏህ አከበር**

አሏህ በጣም ትልቅ ነው (እያንዳንዱን ጠጠር ከወረወሩ ቡኃላ)፡፡ የመጨረሻው ጀመራህ ላይ ከወረወሩ በኃላ ዱዓ ሳያደርጉ ወደ ፊት ይንቀሳቀሱ፡፡

**የዙልሂጃህ አስራሁለተኛው ቀን**

## የዙልሂጃህ አስራሁለተኛው ቀን

- ጠዋፉል ኢፋዳህ እስከዚህ እለት ድረስ ካልተደረገ መካ ሄደው ጠዋፍ ያድርጉ፡፡ ሁለት ረከዓ ይስገዱ፣ ከዘምዝም ይጠጡ ከዛም ሰዕይ ያድርጉ፡፡ ወደ ሚና ይመለሱ፡፡
- ከዘዋል (ከእኩለ ቀን በኃላ) አንስቶ እስከ ለሊት ባለው ጊዜ ወስጥ እያንዳንዱ ጀመራት ላይ ሰባት ፤ሰባት፤ሰባት ጠጠር( በድምሩ 21 ጠጠር)ይወርወሩ፡፡ ፡፡ ከታቻለ ፀሀይ ከመጥለቋ በፊት ከሚና ወደ መካ ይሂዱ መሄድ ካልቻሉ ሚና ይቆዩ፡፡

## የዙልሂጃህ አስራሶስተኛው ቀን

- ከፈጅር በኃላ ካለው ጊዜ ጀምሮ ከሚና ካልወጡ እያንዳንዱ ጀመራት ላይ ሰባት ፤ሰባት፤ሰባት ጠጠር( በድምሩ 21 ጠጠር)ይወርወሩ፡፡
- ወደ መካ ይሂዱ

ከመካ ከማሰናበትዎት በፊት ጠዋፉል ወዳዕ (የማሰናበቻ ጠዋፍ) እንደመጨረሻ ተግባር ያድርጉ ፡ጠዋፉል ወዳዕ በዙልሂጃ 12ኛው ቀን ማድረግ ይቻላል (ፀሀይ ከመጥለቋ በፊት ሚናን እስከለቀቁ ድረስ)፡ይህን ማድረግዎት ግን የሚወደደውን (ነገር ግን ግዴታ ያልሆነውን) ጠጠር የመወርወሪያ ቀን ያሳጣዎታል፡፡

### በሀጅ ወቅት በሜሬት ወስጥ የከተማ ባቡር ማዓዝ




በሜሬት ወስጥ የከተማ ባቡር የሚጠቀሙ ሀጃጆች የሚሳፈሩት እና የሚሳት ከአረፋት፣ መዝደሊፋ፣ ሚና እና ጀመራት ነው፡፡ ለሀጃጃቹ በሚሠጠው የእጅ አንባር ከለር(ቀለም) ላይ ተመስርቶ እያንዳንዳቸው የድንኳን ቅርፅ ያላቸው ሶስት ሶስት(በድምሩ ዘጠኝ) ጣቢያዎች አላቸው፡፡ (ከለር ያላቸው አንባሮች ከሀጅ በፊት ለሚሄዱ ሀጃጆች ይሰጣሉ፡፡

Amharic **አማርኛ إثيوبيا، الأمهرية**

رقم اذن بطبع ٥٢٠٩/م /ج في ١٤٣١/١٢/٣٠